# “አይነጋ፡መስሏት፡ታንቀላፋለች”።

፩-፫ ጥቅምት፡፲፰፡ቀን፡፪ሺ፬፡ዓመተ፡ምሕረት።






“ድር፡ቢያብር፡አንበሣ፡ያሥር”።ያሉበት፡ምክንያት፡አንዷ(ዱ|)፡ክር፡ከብዙዎች፡ክሮች፡ጋራ፡ሆነው፡አንበሣው፡ሲታሠር፡ሊበጥሰው፡ባለ፡መቻሉ፡ይሸነፋልና፡ማጥቃትን፡ያበሥራል።ስለዚህ፡እኔ፡የሚለው፡ብቼኛና፡ተጠቂ፡ቃል፡ከእኛ፡ጋራ፡ቢያብር፡ድልን፡ስለ፡እሚቀዳጅ፤እያንዳንዳችን፡እኔ፡ብለን፡ለትግሬ፡ወያኔው፡ዐመፀኛ፡አምባገነን፡ለገሠ፡ዜናዊና፡አብሯደግ፡ደጋፊዎቹ፡መልእክት፡እንደ፡እሚከተለው፡ለመግለጽ፡ያሠብነውን፡ብትተባበሩን፡ምን፡ይመስላችኋል?፡-

ጨካኙና፡አረመኔው፡ለገሠ፡ዜናዊ!፡በደጉ፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ላይ፡አትቀልድ።በጊዜ፡እርማት፡ማድረጉ፡መልካም፡ይመስለኛል።አገራችን፡ሰው፡አጣች።ዕድሜ፡ለመንግሥቱ፣አዲሱ፡ትውልድም፡ችግሩ፡ሲጠናበት፡ተስፋ፡በመቁረጥ፡ተመርሮ፡የአገር፡ፍቅር፡የሌለው፡ለሆዱ፡ያደረ፡አውደልዳይ፡ከንቱ፡ፍጥረት፡በመሆኑ፡የወያኔ፡መጫዎቻና፡ከቆሻሻ፡ለቅሞ፡በመመገብ፡ተዳዳሪ፡አደረገው።የእህል፡ረሃብ፡ብቻ፡ሳይሆን፡የነፃነትና፡ጠንካራ፡መሪም፡ረሃብተኞች፡አደረገን።ኧረ!፡ተው።የሚልህ፡ሰው፡ጠፋ።ጣዖት፡ጳውሎስም፡የአምላካችንን፡ትዛዝ፡በማሰማት፡ፈንታ፡ግድ፡የለሽ፡ካድሬ፡ስለ፡ሆነ፡ዝም፡ብሎ፡ይመለከታል።አንተ፡ለገሠ፡ዜናውም፡ኢትዮ|ጵያን፡አዘቅት፡በማውረድ፣የሕዝቡን፡መብት፡በመግፈፍ፡በዬ፡ጊዜው፡ያመቻቸኸው፡አሸባሪ፡ዐዋጅ፡በችግር፡ላይ፡ችግር፣ለረሃብና፡ሥቃይ፡የዳረግኸው፡የኢትዮ|ጵያ፡ሕዝብ፡ምን፡ስለ፡አደረገህ፡ነው?።አንተ፡ከጥቂት፡አበሮችህ፡ጋራ፡እዬ፡ተንድላቀቅህ፡አገሪቱን፡ለማውደም፡ቀንና፡ሌሊት፡ተንኮልህን፡በሺህ፡በማባዛት፡መሮጥህ፡ያስገርማል!።አምላኩን፡ተማጽኖ፡የሚኖረውን፡ጅግና፣ቅንና፡ደግ፡የሆነውን፡የኢትዮጵያን፡ሕዝብ፡አትጫወትበት!።በሺህ፡በሚቆጠሩ፡የጸጥታ፡ጠባቂ፡ተከቦ፡ይጐላመም፡የነበረው፡ብጤህ፡ትዕቢተኛው፡መሐመድ፡ጋዳፊ፡እንኳ፡የደረሰበትን፡ዓይተሃል።እርሱ፡፵፪፡ዓመታት፣አንተም፡፳፡ዓመታት፡በማን፡አለብኝ፡በአምባገነንነት፡ቆይታችኋል።የሊቢያ\፡ሕዝብ፡እፎይ፡ሲል፡የኢትዮጵያን፡ሕዝብ፡ማሠቃዬት፡ደስታህ፡አድርገህ፡ይዘኸዋል።ዛሬ፡ከአበሮችህ፡ጋራ፡ትጨማለቃለህ።ጊዜው፡እሩቅ፡አይደለምና፡አታመልጥም።የመሐመድ፡ጋዳፊን፡ግንባር፡ዓይተኸዋል።አንድ፡ቀን፡የመረረው፡ጀግና፡ያከናንብሃል።ስለዚህ፡የአምባገነኖች፡መጨረሻ፡ምን፡እንደ፡ሆነ፡ለማስታዎስ፡ያለፉትን፡ሂትለርን፣ሙሶሊኒን፣የቅርቡን፡ሳዳም፡ሁሴንንና፡መሐመድ፡ጋዳፊን፡ዓይተህ፡በጊዜ፡መታረሙ፡ይሻልሃል።

ለገሠ፡ዜናዊ!፣ካንተ፡አመራር፡ጋራ፡አያይዠ፡ለማስታዎስ፡የምፈልገው፡የቀድሞ፡ጓደኞችህ፡የዛሬው፡ተቃራኒዎችህ፡ብርሃኑ፡ነጋንና፡አንዳርጋቸው፡ጽጌ፡አመሪካና፡እንግሊዝ፡አገር፡ተቀምጠው፡

ሌላው፡መሥዋዕት፡እንዲሆን፡ይሻሉ።አንተ፡ለገሠ፡እንዳደረግኸው፡ከለንደን፡በረህ፡አዲስ፡አባባ፡መጥተህ፡ማንም፡ሳይወክልህ፡ባሕረ፡ምድርን፡አስገንጥለህ፡ኢሳያስን፡በዘዴ፡አባረህ፡ሥልጣኑን፡እንደ፡ያዝህ፡ሁሉ፤በተመሳሳይ፡ብርሃኑና፡አንዳርጋቸውም፡ሌላው፡ደሙን፡ባፈሰሰ፡ሥልጣን፡ለመያዝ፡ጉጉት፡እንዳሰከራቸው፡ነው።አንተ፡ለገሠ፡ዜናዊና፡አበሮችህ፡እነ፡ስብሐት፡ወልስደ፡ሥላሴ፡ነጋ፣በረከት፡ስምዖን፣ስዩም፡መስፍን፣ስየ፡አብርሃ፣ገብሩ፡አሥራት፣መድረክ፡ውስጥ፡ሕዝብን፡ለማወናበድ፡ወ፣ዘ.ተ........ኢትዮጵያንና፡ሕዝቧን፡ከመከራ፡ረሃብና፡ችግር፡ላይ፡እንደ፡ጣላችኋት፡ሁሉ፣ብርሃኑና፡አንዳርጋቸውም፡ከአንተና፡አበሮችህ፡በየትኛው፡ተግባራቸው፡መለየት፡ይችላሉ?።ስለዚህ፡“ከእጅ፡አይሻል፡ዶማ”፡ናቸው።እግዚአብጤር፡የሚበጀውን፡ለአገሪቱና፡ሕዝቧ፡ያምጣላት፡እላለሁ።ርሃኑንና፡አንዳርጋቸውን፡በመጥቀሴ፡የመስበኪያ፡ዒላማህ፡እንዳታደርገው፡ተጠንቀቅ።ግልጽ፡ያልሆነልኝን፡አቋማቸውን፡ባስተማማኝ፡ሲያስተካክሉና፡ላለፈው፡ስሕተታቸው፡የኢትዮጵያን፡ሕዝብ፡ይቅርታ፡ጠይቀው፡ንሥሐ፡ሲገቡ፡ከጐናቸው፡እሰለፋለሁ።አንተ፡ግን፡ከ፳፡ዓመታት፡በኋላ፡ድክመትህ፡ያለህ፡አማራጭ፡በሰላም፡ሥልጣንህን፡መልቀቅ፡እንደሚሆን፡አልጠራጠርም።እስተዚያ፡ግን፡በእኔ፡አመለካከት፡የኢትዮጵያዊነቴን፡ድርሻ፡ለመወጣት፡ማንነታቸውን፡ለሕዝብ፡ማመልከቱን፡መርጫለሁ።

ብርሃኑ፡ነጋ፡ኔዘርላንድ፡እንደራሴ፡ጽሕፈት፡ቤት፡ሄደህ፡ፍላጐትህን፡ተነጋግረህ፡ከወጣህ፡በኋላ፡-ቅንጅትን፡ያፈረስህ፣የሕዝብን፡ምኞት፡ያኮላሸህ፡የትግል፡ጠላት፡መሆንህን፡አትርሳ።እነ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡የቀድሞ፡የጫካ፡ጓደኞችህ፡ስለ፡ሆኑ፡እነርሱ፡በአሁኑ፡ጊዜ፡የሚፈጽሙትን፡ግፍ፡ገበሬውን፡እዬ፡ነቀሉ፡ለም፡መሬቱን፡ለቻይና፣ለሕንድ፡ለዓረብና፡ለኢንዶኔዚያ፡ወ.ዘ.ተ......ሀብታሞች፡ሲሸጡ፡ምን፡ተናገርክ?።ሕዝቡን፡ሲያስርቡትና፡ሲያሠቃዩት፡ምን፡አደረግህ?።በዝምታ፡አይደለም፡እንዴ፡ያለኸው!!።ስለዘህ፡ለሥልጣን፡ከመሮጥ፡ውጭ፡ለኢትዮጵያና፡ሕዝቧ፡ምን፡የተለዩ፡ነገር፡ታመጣለታለህ?።ለ፴፰፡ዓመታት፡ስለ፡ተጨቆነ፣ተሠቃዩና፡ተጨፈጨፈ፡የኢትዮጵያን፡ሕዝብ፡አንገፍግፎታልና፡ማንም፡አያምንህ።ያለፈውም፡ሆነ፡ዛሬ፡ያለው፡ለአገሪቱ፡አልበጀም።ወደ፡ፊትም፡ሁሉን፡ማድረግ፡የሚችለው፡አምላክ፡ኢትዮጵያንና፡ሕዝቧን፡ለመምራት፡እራሱን፡የማይወድ፡ታማኝ፡መሪ፡ያመጣላታል፡ብዬ፡ተስፋ፡አደርጋለሁ።ብርሃኑም፡አንተንና፡አንዳርጋቸውን፡የመሰሉ፡መላው፡የጠፋባቸው፡የሚዘላብዱ፡ወሬኞች፡ከኋላችሁ፡እንዳሉ፡ሁሉም፡ሰው፡ያውቃል።እነዚህ፡ሰዎች፡ስለ፡እናንተ፡ያልተረዱና፡ያልገባቸው፡ናቸው።ስለዚህ፡ነው፡“ከእጅ፡አይሻል፡ዶማ”፡ያልኩት።እሩጫችሁ፡ለሥልጣን፡እንጂ፡ኢትዮጵያንና፡ሕዝቧን፡በታማኝነት፡ለማገልገል፡የተዘጋጃችሁ፣ሰላምንና፡ደህንነትን፡ለመምጣት፡እንዳልሆነ፡ሳይታለም፡የተፈታ፡ነው።የማያውቃችሁ፡ማን፣ለምን፡እንደ፡ሆነ፡ይወቃችሁ።

አታጋይ፡መሪ፡ለመሆን፡ከሕዝቡ፡መካከል፡ተገኝቶ፤ስሜትና፡ፍላጐቱን፡በመመዝገብ፡እንጂ፡ተራርቆ፡እኔ፡ዐውቅልሃለሁና፡እመነኝ፡ማለት፡ያዳግታል።ከሕዝቡ፡መካከልም፡የታወቀ፡ጐበዝ፡አለቃ፡መልምሎ፡የትግሉን፡ስልት፡ማጥናት፡ያስፈልጋል።ለሥነ፡መንግሥታዊ፡ትግል፡መቀሳቀሻ፡የተሟላ፡ንብረትና፡ድጋፍ፡ሊኖር፡ይገባል።እራሱን፡ማስተዳደር፡ያልቻለና፡በእንግሊዝ፡መንግሥት፡የኑሮ፡መደጐሚያ፡ተዳዳሪ፡ለሙስና፡ተጋላጭ፡ሊሆን፡ይችላልና፡ብቃት፡ያለው፡መሪ፡መሆን፡አይችልም።አንዳርጋቸውም፡ቀሪው፡ወገናችን፡ሰላምና፡ፍትሕ፡በተጓደለበት፡አስተዳደር፡መሥራት፡እንደማይቻል፡በማሠብ፡ውጭ፡አገር፡እዬ፡ኖርክ፡ሳለህ፤በእሳት፡ጎዋ፡ሰሌዳ፡እንደገለጽከው፡፤የትምህርት፡ቤት፡ጓደኞችህ፡ሥልጣን፡መያዛቸውን፡አረጋግጠህ፡ወደ፡አገራችን፡ተመለስክ።ገብተህም፡የአስተዳደር፡ተብያቸው፡ማጠናከሪያ፡ስብከት፡(ፕሮፖጋንዳ)፡ኃላፊነት፡ሥልጣን፡ተሰጥቶህ፡አጠናከርካቸው።ከዚያም፡በፊት፡ለንደን፡በሚገኘው፡ቢሯቸው፡አገር፡ለማስገንጠል፡ይዘጋጁ፡በነበሩበት፡ወቅት፡ግንኙነት፡እንደ፡ነበረህ፡ገልጸሃል።የትብብርህ፡ውጤቱም፡እንሆ!፡ባሕረ፡ምድርን፡ከእናቷ፡ለይተው፡እናቷን፡የባህር፡በር፡አልባ፡ሆና፡በዝግ፡ቤቷ፡እንድትቸገር፡የታቀደውን፡ተግባራዊ፡አስደርገሃል።አብረሃቸው፡በሥልጣን፡ላይ፡ጉዞ፡ለመዝለቅ፡እንዳሰብከውም፡ሳይሆኑና፡የትግሬ፡ጐጠኛነታቸውን፡ኃይል፡አጠናክረው፡መፈናፈኛ፡ስላሳጡህና፡ታሥረህ፡ስትፈታ፡እንደ፡ገና፡ወደ፡ውጭ፡አገርህ፡ወጣህ።፳፡ዓመታት፡ጓደኖችህ፡በሙስና፡ሲጨማለቁ፣የባንክ፡ዘራፊዎች፣አላፊ፡አግዳሚውን፡እያቆሙ፡ዘራፊዎች፡ወ.ዘ.ተ......እንደ፡ሆኑ፡ማወቅህን፡እዬ፡ተናገርክ፡በማጋለጥ፡ኢትዮጵያ፡ውስጥ፡በተወለድክበትና፡በምታውቀው፡ጫካ፣ዋሻ፡ወ.ዘ.ተ...........

አሻፈረኝ፡በማለት፡ተከታይ፡መልምለህ፡መታገል፡ሲገባህ፤ውጭ፡ሆነህ፡ሙቱልንና፡ሲሰላ፡ገብተን፡
እናስተዳድር፡ብላችሁ፡ብርሃኑ፡መሪ፣አንተ፡ተመሪ፡ዋና፡ጸሐፊ፡ሆናችሁ፡የምትንቀሣቀሱት፡አግባብ
ነት፡የሌለው፡ነው።አዲስ፡አበባ፡በጎቡዕ፡ለመንቀሣቀስ፡ያሡቡትም፡ኑና፡ቁጭ፡ብለን፡ተነጋግረን፡የሚ
ሆነውን፡እናዘጋጅ፡ቢሏችሁ፡ገንዘብ፡መላክ፡እንጂ፡ገብቶ፡የመታገል፡ፍላጎት፡እንደሌላችሁ፡ብሎም፡ከ
እኛ፡ጋራ፡ካልተሰለፋችሁ፡ገንዘብ፡አንሰጣችሁም፡ያላችሁት፡ልክ፡የአረመኔው፡ትግሬ፡ወያኔ፡ዐመፀኛ፡
አምባገነኑ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡ስልት፡ጋራ፡ተመሳሳይ፡መሆኑ፡ያው፡ለይስሙላ፡እንጂ፡ውስጥ፡ውስጡን፡አብ
ራችሁ፡የጥቅም፡ታጋሪዎች፡እንደሆናችሁ፤ያመለክታል።

ሕዝብ፡እንዲደግፋችሁ፡ከፈለጋችሁ፡ግቡና፡ውጭ፡አገር፡እንደ፡እምትናገሩት፡ትጥቅ፡ትግሉን፡
አፋፍሙት።ከውጭ፡አገር፡መንግሥታት፡ጋራ፡እንደነ፡አረመኔው፡ለገሠ፡ዜናዊ፡እግር፡አጥባችሁ፡ለመሳ
ሙ፡ደጅ፡ጥናት፡ዕቅድ፡ይቅርባችሁ።ዓላማችሁም፡የመንግሥታቸውን፡ጥቅም፡አስጠባቂ፡መርዎች፡ደ
ግፈው፡ሥልጣን፡ላይ፡እንዲያስቀምጧችሁ፡ለመጠርጠር፡የሚከፈላችሁ፡ድጐማ፡እያመለከተኝ፡ነው።
የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ጠካራና፡ጀግና፣ቆራጥና፡አስተዋይ፡ነው።የሚፈልገውም፡ጥሪትና፡ቆራጥ፡አዋጊ፡መ
ሪ፡ነው።ስለዚህ፡የሚያዋጣው፡ከሕዝብ፡ጐን፡ቁሞ፡በማስተባበር፡መነሣቱ፡ብቻ፡ነው።“በለፈለፉ፡ይጠ
ፉ”፡ነውና፡ውጭ፡አገር፡ሆናችሁ፡ስትለፈልፉ፡አገር፡ቤት፡ያሉትን፡አባቶቻችሁንና፡ወገኖቻችሁን፡ባሸባ
ሪነት፡ከማስፈረጅ፡በስተቀር፡ሌላ፡አዋጭ፡ትርፍ፡አይኖረውም።አላገኘምም።

እግዚአብሔር፡ለኢትይጵያና፡ሕዝቧ፡ደጉንና፡ደጋጉን፡ያምጣላት።

# ኢትዮጵያ፡ለዘላለም፡ትኖራለች።

ከዜናማርቆስ፡መርሐ፣ካናዳ።

እ፡ጦማር፡-zienamarqos@yahoo.com